# በወ/ት ብርቱካን ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍ ሁላችንም እንቅልፍ ሊነሳን ይገባል

**ከግንቦት7 የተሰጠ መግለጫ**

መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ. ም

በአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ቀጭን ትእዛዝ በቃሊቲ እስር ቤት በግፍ ታስራ የምትገኘው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የጤንነት ሁኔታ አሳሳቢ በሆነ ደረጃ ላይ መገኘቱን ለመረዳት ችለናል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ ያደረጉላት ዶክተሮች ተጨማሪ ህክምና እንደሚያስፈልጋት ቢያሳስቡም፣ በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ትእዛዝ ህክምና የማግኘት ሰብአዊ መብቷን እንደተገፈፍ ተደርጓል።

አረመኔው መለስ ዜናዊ ስለ ወ/ት ብርቱካን የጤና ሁኔታ ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ "ትንሽ ክብደት ከመጨመሯ በስተቀር በጣም ደህና ነች ቤተሰቦቿም ይጠይቋታል" ሲል ለመሳለቅ ሞክሯል። ብርቱካን ከአመት በላይ በቆየችበት እስር ቤት ከስድስት ወራት በላይ እጅግ ጠባብ በሆነች ክፍል ውስጥ በብቸኝነት እንድትታሰር ተደርጓል። እንዲሁም የ70 ዓመት ባልቴት ወላጇ እናቷና የ5 ዓመቷ ህጻን ልጇ በየሳምንቱ ለ30 ደቂቃ እንዲጎበኟት ከመደረጉዋ በስተቀር፣ ከሰው ተገልላ የስነ ልቦና ስቃይ እንዲደርስባት እየተደረገ ነው። ይህ ሁሉ ግፍ የሚፈጸምባት በአንድ ምክንያት ብቻ ነው- ለእውነት በመቆሟ።

ወ/ት ብርቱካን በአምባገነኖች ትእዛዝ ወህኒ እንድትወርድ ከተደረገችበት ጊዜ ጀምሮ፣ የግንቦት7 ንቅናቄ የወያኔን አገዛዝ ድርጊት በማውገዝ ተደጋጋሚ መግለጫ ሲያወጣ ቆይቷል፤ ብርቱካን ምንም አይነት ወንጀል ሳትሰራ በአምባገነኖች ትእዛዝ የታሰረች የህሊና እስረኛ መሆኑዋን፣ ወንጀል አለባት ከተባለም ወንጀሉዋ ለእውነት መቆሟ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲገልጽና የወያኔን እርምጃም ሲያወግዝ ቆይቷል።

እስካሁን ስናደርገው ከነበረው ሁኔታ በተለየ ይህን አስቸኳይ መግለጫ እንድናወጣ ያስገደደንም የጀግናዋ የነጻነት ታጋይ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የጤንነት ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን በመረዳታችን ነው፡፡ በመሆኑም ግንቦት7 ወ/ት ብርቱካን በግፍ ከታሰረችበት እስር ቤት በአስቸኳይ ተለቃ፣ በተሻለ አገር ሙሉ ህክምና የምታገኝበት መንገድ እንዲፈለግ ጥሪ ያቀርባል። የብርቱካን ጉዳይ ማንኛውንም ነጻነት ወዳድ የሆነ/ች ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንቅልፍ ሊነሳው/ት ይገባል እንላለን። ለነጻነት የምንታገል፣ ስለነጻነት የምንዘምር ሀይሎች ሁሉ ወ/ት ብርቱካን በአስቸኳይ ከእስር እንድትፈታ፣ የጀመረችውን ትግል በሙሉ ጤንነት እንድትቀጥል ከዛሬ ጀምሮ ጠንካራ ትግል ማድረግ ይጠበቅብናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**